# መድሎተ አሚን ፡

## የሃይማኖት ሚዛን ።


በመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ተ ዘ ጋ ጀ ።


ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በነገሡ ፡ በ፴፫ኛው ፡
ዘመን ፡ መንግሥት ፤

ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የኢትዮጵያ ፡
ፓትሪያርክ ፡ በሆኑ ፡ በ፭ኛው ፡ ዓመት ፤


ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ. ም.

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ/ም
በድጋሚ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡

ኢትዮጵያውያን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ አመዛዝነው ፡ ብልጫና ፡ ላቂያ ፡ ያለው ፡ መኾኑን ፡ የሚረዱበት ፡ ስለኾነ ፡ የሃይማኖት ፡ ሚዛን ፡ ተብሎ ፡ ተሰየመ።



የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ

አዝማች አስፋ ወሰን ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት
ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ።

# ማ ው ጫ


መቅድም ፲፯
መግቢያ ፳፪
ማቅረቢያ ፳፫
የደራሲው ፡ ዐጭር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፳፯
መልስ ፡ የሚሰጥበት ፡ መቅድም ፳፰
ደራሲው ፡ የጠቀሷቸው ፡ መጻሕፍት ፴፬
በኢትዮጵያ ፡ የሚታመነው ፡ ባህል ፴፯
እውነተኛው ፡ ምክንያት ፵፩
ኢትዮጵያ በእስክንድርያ ፡ ስለመመራቷ ፵፬
ስለግብጻዊው ፡ ጳጳስ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ፵፱
ነገሥታቱ ፡ በሃይማኖት ፡ስላላቸው ፡ ሥልጣን ፶፩
ስለ ፡ ዕጨጌው ፡ ሥልጣን ፶፫
ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ መቼ ፡ ነው ፷፪
ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ፷፫
በይኾናል ፡ የሚገለጹ ፡ አሳቦች ፷፬
ስለ ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ አመጣጥ ፷፭
የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ የመቃወም ፡ ምልክት ፸፪
ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አስተያየት ፹፯
በጉባኤ ፡ ስለተደረገው ፡ ታሪክ ፡ ስሕተት ፺
አካላዊ ፡ ተዋሕዶን ፡ ሲተረጕሙ ፡ የሚያገቧቸው ፡ ቃላት ፻፲፩
የቃሎች ፡ ምርመራ ፻፲፫
የኬልቄዶኑን ፡ ውሳኔ ፡ ይቀበላሉ ፡ ስለሚሉት ፻፳፭
የኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎች ፡ ክርክር ፻፵፯
የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፻፵፱
የመጀመሪያ ፡ ክርክሮች ፻፶፪
በ፲፯ና ፡ በ፲፯ኛ ፡ ፻ ፡ የተደረጉ ፡ ክርክሮች ፻፶፫
አሳቦችና ፡ ምስክሮች ፻፷፯
በአምልኮና ፡ በሃይማኖት ፡ የሚገኝ ፡ ትምርት ፻፸
ስለክርስቶስ ፡ ቅብዐት ፡ ክርክር ፻፸፱
ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፻፸፱
የተገለጡ ፡ አስተያየቶች ፻፺፭
የርስ ፡ በርስ ፡ ክርክሮች ፻፺፪
ስለቅኔዎች ፻፺፫
የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፪፻፲፭
ጠቅላይ ፡ መደምደሚያ ፪፻፲፯
ማጠቃለያ ፡ አሳብ ፪፻፳፱

# መቅድም ፡፡

## ከመልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ የተዘጋጀ ።

መቅድም ፡ ማለት ፡ ለሚመጣው ፡ ነገር ፡ መሪ ፡ ፊታውራሪ ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ይደልዎ ፡ ለዘያነብብ ፡ ቅድመ ፡ ይዝክር ፡ ስሞ ፡ ለበዓለ ፡ መጽሐፍ ፡ ወእምዝ ፡ ያንብብ ፡ ወይምሀር ።

መጽሐፍ ፡ ለሚመለከት ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ የደራሲውን ፡ ስምና ፡ ታሪክ ፡ ማወቅ ፡ ከዚያ ኋ በኋላ ፡ መጽሐፉን ፡ ማንበብ ፡ መተርጐም ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ እንደነገረን ፡ እኔም ፡ አስቀድሜ ፡ ስሜንና ፡ አድራሻዬን ፡ ቀጥዬም ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሰብኩበትን ፡ ምክንያት ፡ እያከታተልኩ ፡ እጽፋለሁ ።



እኔ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀንበሬ ፡ የተወለድኩበትና ፡ ያደግሁበት ፤ የተማርኩበት ፤ ሀገሬ ፡ በጎጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፤ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ ተብዬ ፡ የተሾምኩበት ፡ ብቸና ፡ ጊዮርጊስ ነው ።

እውነተኛ ፡ ትምህርት ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ለራሱም ፡ ለሀገርም ፡ ነው ፡ ያገርን ፡ ልማድ ፡ እያስንቅም ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ እያርቅም ፡ በባሕርይ ፡ ጠማምነት ፡ የተሸፈነ ፡ ትምህርት ፡ ግን ፡ ጎጂ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ መጋቢት ፡ ፳፭ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቀ-ኃ-ሥ ፡ » የሚለውን ፡ ንጉሣዊ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ተመርኩዘን ፡ ከባቶቻችን ፡ ያገኘነውን ፡ ባህል ፡ ንቆ ፡ ከመጣል ፡ እንጠበቅ ።

«በአእምሮ ፡ ጠንክሩ ፤ በሥራ ፡ ጠንክሩ ፤ በሃይማኖት ፡ ጠንክሩ ፤ የመጨረሻውን ፡ ዕድልና ፡ የድል ፡ አክሊል ፡ ትወርሳላችሁ ።» ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ/ም ። የሚለውን ፡ ንጉሣዊ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ከባቶቻችን ፡ በወረስናት ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ ተገኝተን ፡ የመጨረሻውን ፡ የድል ፡ አክሊል ፡ ለመቀዳጀት ፡ ያብቃን ፡ አሜን ።



ይህ ፡ ሥዕል ፡ ሮማ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ የቁልቁሊት ፡ ሰቅላ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ በሰይፍ ፡ መትራ ፡ እንደ ፡ ገደለቻቸው
ያሳያል ። ሮማ ፡ ይህን ፡ ትሠራ ፡ በነበረበት ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ነዋ ፡ ማይ ፡ መኑ ፡ ይከልዓኒ ፡ ተጠምቆ ።
ውን ፡ እነሆ ፡ አለ ፤ መጠመቅን ፡ ማን ፡ ይከለክለኛል፡ብላ፡ በፈቃዷ ፡ ወንጌልን ፡ መቀበልን ፡ ጀምራለች ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፴፮-፴፰

ጳጳስ ፡ ማስመጣቷ ፡ ቀርቶ ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ ከተወላጆቿ ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ፓትርያርክ ፡ ለመሾም ፡ ችላለች ፡ ከሮማና ፡ ከሌሎችም ፡ ሀገሮች ፡ ጋራ ፡ በአየርም ፡ በባሕርም ፡ ቢኾን ፡ ያለችግር ፡ ለመገናኘት ፡ ች ለች ፡ አሁን ፡ አትቀበላትም ፡ ኖሯልን ፤ የለም ፡ ይህ ፡ የሚናገሩት ፡ ኹሉ ፡ ማስመሰል ፡ ማታለል ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።